መልእክት አሥር

## እግዚአብሔርን የመምሰል (godly) ሕይወት መኖር

የመጽሐፍ ቅዱስ ንባብ ክፍል፡- ምሳ. 29፡18፤ 23፡23፤ 20፡27፤ 4፡23፤ 10፡12፤ 17፡9

### I. "ራእይ ባይኖር ሕዝብ መረን ይሆናል"—ምሳ. 29፡18፡-

ሀ. በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ራእይ ያልተለመደ ትእይንትን ያመለክታል፤ ልዩ የሆነን ማየት—የከበረ፣ ውስጣዊ ማየትን—እና ከእግዚአብሔር ዘንድ የምናየውን መንፈሳዊ ትዕይንት ያመለክታል—ሕዝ. 1፡1፣ 4-28፤ ዳን. 7፡1፣ 9-10፣ 13-14።

ለ. ራእይ እንዲኖረን፣ መገለጥ፣ ብርሃን፣ እና ዓይነ-ብርሀን ያስፈልገናል—ኤፌ. 1፡17-18።

ሐ. ሰማያዊው ራእይ ይገዛናል፣ ይገድበናል፣ ይቆጣጠረናል፣ ይመራናል፣ ጠብቆ ያቆየናል፣ ሥር-ነቀል በሆነ መልኩ ይለውጠናል፣ በእውነተኛው አንድነት ውስጥ ይጠብቀናል፣ ወደፊት እንድንሄድ ድፍረትን ይሰጠናል—ምሳ. 29፡18።

መ. ይህንን ራእይ ስናይ መላው የውስጡ ማንነታችን ውስጣዊ የሆነ መዞር ያገኛል፣ እንዲሁም በአስተሳሰባችን፣ በጽንሰ-ሃሳባችን እና በአኳኋናችን እንለወጣለን።

ሠ. ሰማያዊው ራእይ ያነሳሳናል፣ ያበረታናል፣ ይይዘናል፣ ጽናትን ይሰጠናል፣ ወደ ጌታ የአሁን እንቅስቃሴ ውስጥ ያመጣናል፣ ሕይወታችን በትርጉምና በአላማ የተሞላ እንዲሆን ያደርገዋል—ዕብ. 1፡8፤ 12፡1-2፤ ኤፌ. 3፡11፤ 2 ጢሞ. 1፡9፤ 3፡10፤ ራእ. 1፡9፤ 3፡10።

ረ. ጌታን የሚያገለግል እያንዳንዱ ሰው ራእይ ያለው ሰው መሆን አለበት፤ ውስጣዊው ራእይ ጌታን የምናገለግልበትን መንገድ ሥር-ነቀል በሆነ መልኩ ይለውጠዋል—ሐዋ. 26፡13-19፤ ሮሜ 1፡9።

ሰ. በሰማያዊው ራእይ ሥር ወደ እግዚአብሔር መዳረሻ ተመርተናል፣ ሕይወታችንም በእግዚአብሔር ኢኮኖሚ መሠረት ቁጥጥር ሥር ነው—ፊልጵ. 3፡13-14፤ 1 ጢሞ. 1፡4።

ሸ. የመጽሐፍ ቅዱስ ገዢው ራእይ በአዲሲቱ እየሩሳሌም የምትጠናቀቀውን የክርስቶስን አካል ለማፍራትና ለመገንባት መላው ማንነታቸውን በመለኮታዊው ሥላሴ ፈጽሞ ለመሙላት ሦስታንዱ አምላክ ወደ መረጣቸው እና ወደ ዋጃቸው ሕዝቡ ውስጥ ራሱን መሥራቱ ነው—ኤፌ. 4፡4-6፤ ራእ. 21፡2፣ 9-10።

### II. "እውነትን ግዛ አትሽጣትም"—ምሳ. 23፡23፡-

ሀ. እውነት ልንገዛት የሚገባ ነገር፣ ዋጋ ያላት ነገር ናት—ቁ. 23፡-

1. መግዛት ዋጋ መክፈልን ይጠይቃል።
2. ጌታን ደስ ማሰኘትና ለእውነት መቆም ከፈለግን፣ ዋጋውን መክፈል አለብን—ተዛ. ራእ. 3፡18።
3. ልቦቻችን የእውነትን ፍቅር ለመቀበል እና በየትኛውም ዋጋ እውነትን ለመግዛት ዝግጁ ከሆኑ፣ እንባረካለን—2 ተሰ. 2፡10-11፤ ምሳ. 23፡23።

ለ. መለኮታዊው እውነት ፍጹም ነው፣ እኛም ለእውነት ፍጹም መሆን እና የእውነትን ፍጹምነት መያዝ አለብን—ዮሐ. 14፡6፤ 18፡37፤ 3 ዮሐ. 3-4፣ 8፡-

1. ለእውነት ፍጹም መሆን ማለት ስሜቶችን ወደ ጎን ማድረግ፣ የግል ግንኙነቶችን ቸል ማለት እና ለእኔነት አለመቆም ማለት ነው—ማቴ. 16፡24-25፣ 1 ጴጥ. 1፡22 ።
2. እውነቱ ልዩና-ብቸኛው መለኪያ ነው፣ ራሳችንን ለመቃወም በእውነት ጎን መቆም አለብን፤ የእውነትን ፍጹምነት መያዝ የሚቻለው ከራሳችን ነጻ የወጣን ጊዜ ብቻ ነው—ዮሐ. 8፡32፤ 2 ዮሐ. 2፤ 3 ዮሐ. 3-4።
3. የእግዚአብሔርን እውነት ማክበር፣ የእውነትን መንገድ መውሰድ እና በምንም አይነት መንገድ እውነቱን አለማመቻመች አለብን—2 ጴጥ. 2፡2።

ሐ. ለመለኮታዊው እውነት መጠናቀቅ፣ ለአሁኑ (ለጊዜው) እውነት ፍጹም መሆን አለብን—1፡12፡-

1. የአሁኑ እውነት (ቅዱሳን) አስቀድመው የተቀበሉትና አሁን የራሳቸው ያደረጉት በቅዱሳን ዘንድ ያለ እውነት ነው—ቁ. 12።
2. የአሁኑ እውነት የዘላለማዊውን የእግዚአብሔር ኢኮኖሚ (ኤፌ. 1፡10፤ 3፡9)፣ የመለኮታዊውን ሥላሴ (2 ቆሮ. 13፡14፣ ራእ. 1፡4-5)፣ ሁሉን-ያካተተውን ክርስቶስ ማንነትና ሥራ (ቆላ 2፡9፤ 16-17፤ 3፡11)፣ የተጠናቀቀው ሕይወት-የሚሰጠውን መንፈስ (ዮሐ. 7፡39፤ 1 ቆሮ. 15፡45፤ ራእ. 22፡17)፣ የዘላለማዊውን የእግዚአብሔር ሕይወት (ዮሐ. 3፡15-16)፣ እንደ የክርስቶስ አካል የቤተ-ክርስቲያንን (ኤፌ. 1፡22-23) እና የአዲሲቱ ኢየሩሳሌምን (ራእ. 21፡2፣ 10-11) ራእይ ያካትታል።

3. የአሁኑ እውነት የመለኮታዊውን መገለጥ ከፍተኛ ጫፍ—አምላክ ሰው ሆነ ተመላኪነቱን ሳይጨምር በሕይወትና በባህሪ ሰው አምላክ ይሆን ዘንድ የሚለውን መገለጥ—ያካትታል፣ ይህም ይህን ዘመን ለመዝጋት እና መንግሥቱን ይመሠርት ዘንድ ክርስቶስን መልሶ ለማምጣት ለሆነው ለእግዚአብሔር ኢኮኖሚ መፈጸም ሕይወታዊዋን የክርስቶስ አካል ለማፍራትና ለመገንባት—ዮሐ. 1፡12-14፤ 1 ዮሐ. 3፡1-2፤ ሮሜ. 8፡3፤ 1፡3-4፤ 12፡4-5፤ ራእ. 11፡15።

## III. "የሰው መንፈስ የእግዚአብሔር መብራት ነው የሆዱን ጉርጆች ሁሉ የሚመረምር"—ምሳ. 20፡27፡-

ሀ. የሰው መንፈስ በሰው ውስጥ ያለ የእግዚአብሔር መብራት ነው—ማቴ. 25፡1፡-

1. ዳግም በተወለደው በሰው መንፈስ ውስጥ የሚያበራው ብርሃን እግዚአብሔር ራሱ ነው—1 ዮሐ. 1፡5።
2. ልክ መብራት (አምፖል) ብርሃንን እንደሚይዝና እንደሚገልጥ፣ የሰው መንፈስ የተፈጠረው እግዚአብሔርን ለመያዝና እርሱን ለመግለጥ ነው።
3. መለኮታዊው ብርሃን ወደ ሰው የውስጥ ክፍሎች ውስጥ ያበራ ዘንድ፣ እንደ ዘይቱ የእግዚአብሔር መንፈስ መንፈሳችንን እንደ ክሩ ማራስ (መዋሐድ) እና ከሰው መንፈስ ጋር አብሮ "መንደድ" አለበት—ሮሜ. 8፡16፤ 12፡11።
4. ለመንፈስ ማብራት ምላሽ ከሰጠን፣ በመንፈስ መሠረት እንመላለሳለን—8፡4።

ለ. የእግዚአብሔር መንፈስም ጭምር ለማብራቱ ሰባት እጥፍ ድምቀት ያለው መብራት ነው—ራእ. 4፡5፡-

1. ዳግም የተወለደው መንፈሳችን ራሱም ጭምር መብራት የሆነው የእግዚአብሔር መንፈስ ያደረበት መብራት ነው።
2. የሰው መንፈስና የእግዚአብሔር መንፈስ ሁለቱም በአንድ ላይ ለውስጡ ክፍሎች አብርሆት የሚሰጡ መብራቶች ናቸው—ምሳ. 20፡27፤ ራእ. 4፡5።
3. መንፈስ ለነፍሳችን እያንዳንዱ ክፍል አብርሆት ለመስጠት ይፈልጋል።

ሐ. ተገቢ በሆነ መንገድ ለመጸለይ መንፈሳችንን ስናንቀሳቅስ፣ የሚያበራ መብራት ይኖራል—ኤፌ. 6፡18፤ 1፡17-18፤ 5፡8-9፡-

1. እየጸለይን ሳለ፣ መንፈሳችን የነፍሳችንን ክፍሎች ሁሉ የሚመረምር የሚያበራ መብራት በመሆን ያገለግላል—ምሳ. 20፡27።
2. አብዝተን በጸሎት መንፈሳችንን ስናንቀሳቅስ፣ አብዝተን ብርሃንን እናገኛለን—2 ቆሮ. 4፡6፡-
   ሀ. መብራቱ በአስተሳሰቦቻችን፣ በስሜቶቻችን እና በፈቃዳችን ላይ ሊያበራ ይችላል።
   ለ. የውስጥ ክፍሎቻችን ጥልቅ-ዝርዝር በሆነ መንገድ በጌታ ይፈተሻሉ (ይመረመራሉ)—መዝ. 139፡23-24።
3. እንዲህ ካለው የጸሎት ጊዜ በኋላ በእግዚአብሔር የተሞላን፣ ብሩህነትና ብርሃን አሳላፊ መሆን ይሰማናል—ኤፌ. 5፡8-9።

## IV. "አጥብቀህ ልብህን ጠብቅ የሕይወት መውጫ ከእርሱ ነውና"—ምሳ. 4፡23፡-

ሀ. ነፍስ ሰውየው (ማንነቱ) ራሱ ስትሆን፣ ነገር ግን ልብ ሰውዬው በድርጊት ማለት ነው—ሉቃ. 1፡66፤ 2፡19፣ 51፤ ሐዋ. 11፡23፤ ኤፌ. 3፡17፤ 1 ተሰ. 3፡13፡-

1. በውስጡ ማንነታችን እኛን የሚወክለን ነገር አለ፣ ይህም ወኪል ልባችን ነው—ሉቃ. 6፡45፤ ዮሐ. 16፡22፤ 2 ቆሮ. 3፡16።
2. ልባችን ራሳችንን የምንገልጥበትና ነገሮችን ለመቀበልና ውድቅ ለማድረግ የምንወስንበት ክፍል ስለሆነ፣ ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ግንኙነት በመጀመሪያ የሚመረኮዘው በልባችን ላይ ነው—ሐዋ. 8፡37፤ ሮሜ. 10፡9-10።
3. ምንም እንኳን መንፈሳችን ንጹህ ቢሆንም፣ ከመንፈሳችን የሚገለጠው ነገር በልባችን ላይ ይመረኮዛል—2 ተሰ. 2፡17፤ 3፡5።

ለ. ልብ የመላው ማንነታችን መግቢያና መውጫ ነች—ማቴ. 13፡19፤ 15፡18-19፡-

1. በማንነታችን ውስጥ የሚካሄደው እንቅስቃሴ (traffic) በልባችን በኩል ስለሆነ፣ እውነተኛው ማንነታችን የሚወጣው በልባችን በኩል ነው—ሉቃ. 6፡45።
2. መንፈሳችን የማንነታችን ምንጭ ሲሆን ልባችን ግን የማንነታችን ልውውጦች የሚተላለፉበት መተላለፊያ፣ መግቢያና መውጫ ነው—ማቴ. 12፡34-35።
3. ተገቢ የሆነ ክርስቲያን ለመሆን፣ መንፈሳችንን ማንቀሳቀስና በንቃት ሁሉ እየጠበቅን ልባችንን መጠበቅ አለብን—ምሳ. 4፡23።

ሐ. በመጽሐፈ ምሳሌ 4፡23 ላይ "ጠብቅ" ተብሎ የተተረጎመው የዕብራይስጡ ቃል "እንደ ዘብ ጠብቅ" ማለት ነው፡-

1. የሕይወት መውጫያዎች ከልባችን ስለሆኑ፣ ከሁሉ በላይ ልባችንን መጠበቅ አለብን።
2. በምሳሌ 4፡23 *መውጫያ* የሚያመለክተው ምንጮችንና ፍልቆችን እንዲሁም መውጣቶችን ነው፡-

ሀ. የሕይወት ምንጮች የሕይወት ወደ ውጪ መፍሰስ ናቸው—ተዛ. ዮሐ. 4፡14።

ለ. ልብ ከሕይወት ምንጮች፣ ከሕይወት ፍልቆችና ከሕይወት መውጫዎች ጋር የተዛመደ ነው—ተዛ. ኢሳ. 12፡3።

ሐ. እኛ የሆንነው፣ የእውነተኛው ማንነታችን ምንጭ ከልባችን ውስጥ ይፈስሳል—ተዛ. ዮሐ. 7፡37-38።

መ. ልባችንን የምንጠብቀው ለልባችን በመጠንቀቅና በሕይወት መንገድ በጌታ ፊት ልባችንን ጥልቅ-ዝርዝር በሆነ መንገድ በማስተካከል ነው፤ አብዝተን ልባችንን ስናስተካከል፣ አብዝተን ልባችንን እንጠብቃለን—መዝ. 26፡2፤ 139፡23-24፤ ምሳ. 4፡23፤ ሮሜ 8፡27፤ ራእ. 2፡23፤ ማቴ. 13፡18-23፤ 5፡8።

ሠ. ለእግዚአብሔር ግንባታ በሕይወት እንድናድግ፣ ጌታን መውደድ፣ ለመንፈሳችን መጠንቀቅ እና በሕይወት መንገድ ላይ ለመቆየት በንቃት ሁሉ ልባችንን መጠበቅ አለብን—1 ጴጥ. 1፡8፤ 2፡2፣ 5፤ 3፡4፣ 15፤ ምሳ. 21፡2፤ 4፡18-23፤ ዘዳ. 10፡12፤ ማር. 12፡30።

**V. "ፍቅር ግን ኃጢአትን ሁሉ ትከድናለች"—ምሳ. 10፡12፡-**

ሀ. "ኃጢአቱን የሚከድን ሰው ፍቅርን ይሻል፤ ነገርን የሚደጋግም ግን የተማመኑትን ወዳጆቹን ያለያያል"—17፡9።

ለ. መሸፈን ፍቅር ነው፤ አለመሸፈን ግን ፍቅር አይደለም—ያዕ. 5፡20።

ሐ. መሸፈን በረከትን ሲያመጣ አለመሸፈን (ማጋለጥ) ግን እርግማንን ያመጣል—ዘፍ. 9፡22-27፡-

1. ሌሎችን የሚያጋልጡ (የማይሸፍኑ) ይረገማሉ።
2. የሌሎችን ኃጢአቶች፣ እንከኖች፣ እና እጥረቶች የሚሸፍኑ ማትረፍን ይደሰታሉ በረከትንም ይቀበላሉ።

መ. "ፍቅር ሁሉን ነገሮች ይሸፍናል" (1 ቆሮ. 13፡7)፣ መልካም ነገሮችን ብቻ ሳይሆን ነገር ግን ክፉ ነገሮችንም ጭምር—

1. "የቤተ ክርስቲያን ሽማግሌዎች በእረኝነት እንክብካቤአቸው የሌሎችን ኃጢአት መሸፈንን፣ የሌሎችን ክፋት አለመቁጠርን መገንዘብ ያስፈልጋቸዋል"—ዘ ቫይታል ግሩፕስ ከሚለው መጽሐፍ፣ ገጽ. 72፡-
   - ሀ. "የቤተ ክርስቲያን አባላትን እንከኖች፣ እጥረቶች እና ኃጢአቶች የሚያጋልጥ ሁሉ ከሽማግሌነቱ ወድቋል"—ገጽ. 72።
   - ለ. "በሽማግሌነታችን ሥር፣ በእረኝነት እንክብካቤአችን ሥር ያሉ ብልቶችን ማጋለጣችን ብቁ መሆናችንን ባዶ ያደርገዋል—ገጽ. 72።
2. በደልን ሁሉ በሚሸፍን ፍቅር በእግዚአብሔር መሠረት ሌሎችን በእረኝነት መንከባከብ ያስፈልገናል—1 ጴጥ. 5፡2፤ ምሳ. 10፡12።

ሠ. "ፍቅር የኃጢአትን ብዛት ይሸፍናልና ከሁሉ በፊት እርስ በእርሳችሁ አጥብቃችሁ ተዋደዱ"—1 ጴጥ. 4፡8።

© 2020 Living Stream Ministry